# ኪ ዳ ና ች ን

# KIDANACH'N

---

## ልዩ ዕትም፤ ነሐሴ ፴ ቀን፥ ፳፻፲፪ (፪ሺ፲፪) ዓመተ-ምሕረት

---

**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥**
**ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳት፣**
**የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ልጆች የኾነውንም ኹሉ፡ ለመጠበቅ፥ ለማሳወቅም፡**
**በ"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት" እየተዘጋጀ የሚወጣ ዕትም።**

**Published by "Ethiopia: The Kingdom of God"**
**to reveal the Divine Truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God**
**and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God;**
**and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.**

---

## "ጳጉሜ"ን እና ሱባዔዋን በሚመለከት፡ ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የተላለፈ ሓተታዊ መልእክት።

---

**አዘጋጅ፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ዓባይነሽ።**

# "ሱባዔ ጳጕሜ"

እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች፡ "ሱባዔ ፍልሰታ" ካበቃች በኋላ፡ ኹለት ሳምንቶችን፡ በሥጋዊውና በመንፈሳዊው የፋሲካ ደስታና የሓሤት ድግስ ቆይተን፡ "ሱባዔ ጳጕሜ"፥ ወይም፡ "የጳጕሜ ሱባዔ" ብለን፡ ከሌሎቹ የዓመቱ አጽዋማታችን መካከል፡ አንዷቱ ኾና የምታስተናግደን፡ ትንሿ ሰሞን ትቀበለናለች። እርሷም፡ በመስከረም ፩ ቀን ለሚውለው፡ ለታላቁ የዐውደ ዓመት በዓላችን፡ ሰሙነ ዋዜማ የኾነችው፡ የዓመቱ መደምደሚያ ጾማችን እና ሱባዔያችን ናት።

## "ጳጕሜ" ምን ማለት ነው?

የ፯ሺ፭፻፲፪ ዓመታት ዕድሜን በሚያስቆጥረው፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን የቀን አቆጣጠር ሥርዓት፡ በግእዝ፡ "**ጳጕሜ**"፥ ወይም፡ "**ጳግሜ**"፥ በሕዝባዊ አነጋገር ደግሞ፡ "ቋግሜ" የምትባለው፡ ግልገል ወር፦

፩ኛ፤ በዐውደ ዓመቱ መጨረሻ የሚገኝ፡ የ፭ (አምስት) ቀኖች ተሩብ "ተውሣክ"፥ ወይም፡ "ጭማሪ" ማለት ነው።

፪ኛ፡ ከዐውደ ወርኅ ስለተረፈና በዓመት መጨረሻ ስለተገኘ፡ "ተረፍ"፥ ወይም፡ "ትርፍ" ይባላል።

በዚህ ቀመር [አቆጣጠር] መሠረት፡ እያንዳንዳቸው፡ እኩል ፴ (ሠላሳ) ቀኖች ያሏቸው፡ ፲፪ (ዐሥራ ኹለት) ወራት፡ የዓመቱን ፫፻፷ (ሦስት መቶ ስድሳ) ቀኖች ብቻ ሲያስገኙ፡ የዓመቱን ዑደት [ዙረት] ፍጹም ምሉእ ለማድረግ፡ በጠቅላላ፡ ፭ (አምስት) ቀኖች፡ ከ፮ (ስድስት) ሰዓቶች ይተርፋሉ። በየ፬ (አራት) ዓመቱ ደግሞ፡ እነዚህ፡ የየዓመቱ ፮ ሰዓታት ሲደመሩ፡ ፳፬ (ሃያ አራት) ሰዓታት ይኾኑና፡ ፩ ቀንን ያስገኛሉ።

ስለዚህ፡ በ፫ቱ (ሦስቱ) ዓመታት፡ ማለትም፡ በዘመናተ ዮሓንስ፥ ማቴዎስና ማርቆስ፡ ፫፻፷፭ቱ ቀኖች እና እንደቅደም ተከተላቸው፡ የዘመነ ዮሓንሱ ፮ (ስድስት) ሰዓቶች፥ የዘመነ ማቴዎሱ ፲፪ (ዐሥራ ኹለት) ሰዓቶች እና የዘመነ ማርቆሱ ፲፰ (ዐሥራ ስምንት) ሰዓቶች እየኾነና እየተደመረ የቀጠለው፡ የየዓመቱ ቀመር፡ በ፬ኛው (አራተኛው) ዓመት፡ በዘመነ ሉቃስ መጨረሻ ላይ፡ ፳፬ (ሃያ አራት) ሰዓቶች ኾኖ በመሙላት፡ ለ፩ (አንድ) ቀንነት ይበቃና፡ ዓመቱን፡ ፫፻፷፮ (ሦስት መቶ ስድሳ ስድስት) ቀኖች ያደርገዋል።[፩]

# የ"ጳጉሜ" አገልግሎት።

ይህችው "ጳጉሜ"፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ ለእግዝእተብሔራችን፣ ለእናታችን እና ለመድኃኒታችን፡ ለድንግል ማርያም፣ ለልጇ፡ ለእግዚአብሔራችን፣ ለፈጣሪያችን እና ለሰላማችን፡ ለመሲሕ ኢየሱስ የልደታት ቀን፡ እንደጾመ ገሃድ እየተቈጠረች፥ ከአሮጌው ዓመት፡ ወደአዲሱ ዓመተ ምሕረትም፡ በንጽሕና እና በቅድስና ተዘጋጅተው የሚሸጋገሩባት፡ ንኡስ የንስሓ ሱባዔ ኾና፡ ስትጾም የኖረች ናት።

ዛሬም፡ እኛ ተከታዮቻቸው፡ የአኹኖቹ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በዚሁ ይዘትና መልክ የምንጠብቃትና የምንገለገልባት፥ የምንጠቀምባትም ኾናልናለች።

መጪዋ የአዲሱ ዓመት፡ መስከረም ፩ ቀን፡ የእየራሳችንን የሰውነት ኹለንተና፡ ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት፡ በንስሓ አድሰን፥ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከድንግል ማርያም በመወለዱ፡ የተገኘውን፡ ዘለዓለማዊዉን የምሕረት ዘመን፡ እንደአዲስ ተሸላሚ፡ የክብር ልብስንና የሕይወት አክሊልን ተቀብለን፡ የምንጐናጸፍባትና የምንቀዳጅባት፡ ቅድስት ዕለት ናት።

ስለዚህ፡ ሊያልቅ በተቃረበው፡ በዚህ ባለንበት፡ የዘንድሮው ዓመት፡ ምናልባት፡ አውቀንም ኾነ ሳናውቅ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ ዐብሮን የቆየ፡ ጎጂና ጥፉ፥ ክፉና ሓሳዊ የኾነ ነገር ቢኖር፡ ያን ኹሉ የተከማቸ የሙስና ጓዝ፡ ካለፈው ዓመት ጋር፡ ከወዲሁ ጥለንና ትተን፥ አስወግደንና አጥድተን፡ ለብቅዓታችን ተዘጋጅተን የምንገኝባት ናት፡ አዎን! ይህች ጳጉሜ።

እንግዴህ፡ መጪዋ መስከረም ፩ ቀን፡-

-የድኅነት እናታችን፡ የእግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም እና የሰላም አባታችን፣ የድል አድራጊው ልጇ፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ የትስብእት ልደቶቻቸው በዓላት የሚውሉባት ስለኾነች፡ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኮ ተቀብለን ልናከብራት ይገባናል፤

-አዎን! ነፍሳችንንና ሥጋችንን፥ መንፈሳችንንም፡ ቅዱስ ቍርባን በኾነው፡ በሥጋ ወደሙ ቀድሰን፡ መላ ሰውነታችንን፡ እንዲህ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ሕይወት የምናበቃባት ልትኾን ይገባል፤

-በአገርነትና በመንግሥትነት፡ የነጻነት በዓሏን፡ በዚያች ዕለት ለምናከብርላት፡ "ኢትዮጵያ" ለተባለችው እናቱ እና�እናታችንም፡ "ዕንቍጣጣሽ! [እነሆ፡ ዕንቍ ለጣትሽ!]" ብለን የደስታ እና የምስጋና ገጸ በረከትን የምናቀርብባት ናት፤

-የአበባ ነዶ እና ጕንጕ አዘጋጅተን፡ እርስ በእርሳችን፡ "የምሥራች! እንኳን አሸጋገረን! እንኳን አደረሰን!" እያልን፡ ደስታችንን የምንለዋወጥባት፡ የተመረጠች፡ የእግዚአብሔር ቀን ናት።

ይህን ዐውቀን፡ ከወዲሁ፡ በዚህ ይዘትና መልክ፡ ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ፡ ከአሮጌው ዓመት፡ ወደአዲሱ ዓመት የምንሸጋገርባትን፡ ይህችኑ ጳጉሜን፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በንኡስ የምስጋና እና የንስሓ ሱባዔነት፡ እነሆ፡ በተለመደው ጾም፥ ጸሎትና ምጽዋት ልናሳልፋት፡ በጉጉት እንጠብቃታለን።

## የጊዜ መሥፈሪያና መቍጠሪያ፡ ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ያስፈልጋቸዋል ወይ?

ለዚህ ጥያቄ፡ መልሱ፡ በቀጥታና ባጭር፡ "<u>***አያስፈልጋቸውም!***</u>" ነው። እነርሱ፡ ጥንት ከመሠረቱ፥ በቅድምናው፡ "የእግዚአብሔር ልጆች!"፥ ኋላም በድምድማቱ፥ በጉልላቱ፡ "የኢትዮጵያ ልጆች!" ስለኾኑ፡ አዎን! አያስፈልጋቸውም።[፬]

ለግዙፉ ፍጥረተ-ዓለም፡ በመዓልት እና በሌሊት እንዲያበሩለት፣ የጊዜ መሥፈሪያና መቍጠሪያም ኾነው እንዲያገለግሉት የተፈጠሩት፡ ፀሓይ እና ጨረቃ፡ ከዋክብትም፡ አዎን! ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት፡ እንዲያበሩላቸው፡ አያስፈልጓቸውም። እንደእግዚአብሔሩ የእውነት ቃላት፡ **የእግዚአብሔር ክብር** ስለሚያበራላቸው ነው። ታዲያ! ይህ የሚያበራላቸው፡ **የእግዚአብሔር ክብር** ማነው? ምንድንስ ነው?

**የእግዚአብሔር ክብርማ፡ "መርዓተ-አብ፥ ወእመ-በግዑ፤** የአብ ሙሽራ፣ የበጉ ልጁ እናት!" እና እናታቸው፣ መድኃኒታቸው እና ሃይማኖታቸው፣ አገራቸው እና ንግሥታቸው የኾነችው፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ናት። **የእግዚአብሔር ክብርማ፡ "ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር፡ ዘየዐትት ኃጢአተ-ዓለም!** የዓለሙን ኃጢአት የሚያስወግድ፡ የእግዚአብሔር በግ" እና አባታቸው፣ ፈጣሪያቸው እና ሰላማቸው፣ ካህናቸው እና ንጉሣቸው የኾነው፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ነው።

እኒህ ኹለቱም፡ የዘለዓለም መብራታቸው ኾነው፡ በሥጋዊው እና በነፍሳዊው፣ በመንፈሳዊው እና በኹለንተናዊው የህልውና ዓለሞቻቸው ውስጥ፡ ያለማቋረጥ ስለሚያበሩላቸው፡ እነርሱ ኹለቱ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በሚመርዋት፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ሥር ለሚኖሩት፡ "የእግዚአብሔር ልጆች!" እና "የኢትዮጵያ ልጆች!" ለኾኑት፣ "የኢትዮጵያ ሕዝብ" ለተባሉትም፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያትና ኢትዮጵያውያን፡ አዎን! ፀሓይና ጨረቃ፣ ከዋክብትም አያስፈልጓቸውም።

የማያስፈልጓቸውም፡ ያለምክንያት አይደለም፤ **"ወኢርኢኩ ጽርሓ፡ እንተ** ከማሃ፣ **እስመ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ ይመልክ፡ ውእቱ ጽርሓ፥ ወበግዑ። ወሀገራሰ ኢትፈቅድ ፀሓየ፥ ወኢወርኀ፡ ከመ ያብርሁ ላቲ፤ እስመ ብርሃነ እግዚአብሔር ያበርህ ላቲ፤ ወማኅቶታ ውእቱ በግዑ።**

"ኹሉን የሚገዛ እግዚአብሔር አምላክና በጉ ኢየሱስ መሢሕ፡ ቤተ መቅደሷ፥ ቤተ ክርስቲያኗ ስለኾኑ፡ ቤተ መቅደስ፥ ወይም፡ ቤተ ክርስቲያን፡ በእርሷ ዘንድ አላየሁም። አገሪቱ፡ የእግዚአብሔር ብርሃን ስለሚያበራላት፥ መብራቷም፡ በጉ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኾነ፡ ፀሓይም፥ ጨረቃም፡ እንዲያበሩላት አያስፈልጓትም።" የተባለው እየተፈጸመ ስላለ ነው።[፫]

ለእግዚአብሔር ይቅርና፡ በዚህ ዓለም፡ በግዘፍ ለምታበራው፡ ለፀሓይም እንኳ ቢኾን፡ ራሷ፡ የብርሃኑ ምንጭ ስለኾነች፥ በዚያ ብርሃኗም ስለተከበበች፡ ለራሷ፡ "በፊትና በኋላ፥ ላይ እና ታች፣ ዙሪያም፣ ትናንት፥ ዛሬና ነገም" የሚባል፡ የቦታ ክልል እና የጊዜ ገደብ፥ ስሌት እና አመዳደብ እንደሌለባት፡ ለማንም ግልጽ ነው።

የሰው ልጆች በፈጠሩት፡ በቅጽበታትና በደቂቃት፥ በሰዓታትና በቀናት፥ በሳምንታትና በወራት፣ በዓመታትና በዘመናት የአቆጣጠር ስልት አማካይነት፡ እርሷ፡ ለሌሎቹ ሥጋውያን፥ ይልቁንም፡ ለሰብአውያኑ ፍጡራን የምታስገኛቸው፡ "ዓምናና ካቻምና፥ ቅድም እና ያለፈ፥ አኹንና በኋላ፥ ትናንትናና ዛሬ፥ ነገና ወደፊት" የሚባሉት የጊዜ ስሌቶች፡ አዎን! ለእርሷ፡ ለፀሓይ አያስፈልጓትም።

እንደዚሁ ኹሉ፡ እነዚህ የጊዜ ስሌቶች፡ በኢትዮጵያ እና በኢትዮጵያ ልጆች ሕይወትና ህልውናም ዘንድ፡ ከቶ አይታሰቡም፤ አያስፈልጉም። ቦታም የላቸውም።

## የጊዜ መሥፈሪያና መቍጠሪያ ሥርዓት ያስፈለጋቸው፡ እነማን ናቸው?

የጊዜ መሥፈሪያና መቍጠሪያ ሥርዓት ያስፈለጋቸውና የፈጠሩት፥ የሚያስፈልጋቸውና እንደፈለጉም የሚያመሰቃቅሉት፡ ጥንት ከመሠረቱ፥ በቅድምናውም፡ "የሰው ልጆች!"፥ ኋላ በድምድማቱ፥ በጕልላቱም፡ "የዲያብሎስ ልጆች!" የተባሉት ናቸው። ለክፋቱ ሥራቸው የሚጠቀሙበት፡ እነርሱ ናቸውና።[፬]

በማናቸውም ረገድ ያለው፡ እግዚአብሔራዊ የኾነው፡ ነፍሳዊውና ሥጋዊው፥ መንፈሳዊውም፡ የሥነ ፍጥረት ህልውናና ሕይወት፣ ምንጊዜም፡ ለመልካሙ ተፈጥሮአዊ ፍሬ ይበቃ ዘንድ፡ የጊዜ መሥፈሪያውና መቍጠሪያው (ቅመራው) ጭምር፡ ከሰይጣናዊውና ከሰብአዊው ክፋትና የተንኰል መርዝ የነጻ መኾን ይኖርበታል።

ይህም ማለት፡ ሥነ ፍጥረትና ፍጥረተ ዓለሙ፡ ፈጣሪያቸው፡ በሠራላቸው ሥርዓት፡ ሳይነኩና ሳይታወኩ፡ በተፈጥሮአቸው፡ እንዲጓዙ ተደርጎ ቢኾን ኖሮ፥ የቅመራውም ዝግጅት፡ በቅዱሱ ኪዳን የእግዚአብሔሩ እውነትና መንፈስ ላይ የተመሠረተ ቢኾን ኖሮ፡ በዚች ምድርና በነዋሪዎቿ ሕያዋን ፍጡሮች ላይ፡ እስከዛሬና ዛሬም፡ እየደረሰ ያለውን ጠንቀኛ የሕይወትና የህልውና ቀውስ ለማስወገድ፥ በዚህም በኩል፡ ገንቢ አስተዋጽኦን ለማበርከት፡ ቀና በኾነ ነበር።

አዎን! በዚህ በተቀደሰ መልክና ኺደት፡ በፀሓይና በጨረቃ፥ በከዋክብትም አማካይነት የሚገኘውና የሚፈራረቀው፡ የዓለሙ ብርሃንና ጨለማ፥ የዕለቱ መዓልትና ሌሊት፥ የወራቱም፡ በጋና ክረምት፥ መፀውና ጸደይ፥ በዐውደ ዓመቱ ዑደት [ዙረት] የሚያበቃው፥ እንደገናም፡ "አንድ ብሎ!" የሚጀምርበት ሥርዓት፡ "ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች" ብቻ ሳይኾን፡ ለሥጋውያኑና ለምድራውያኑ፥ ለዓለማውያኑና ለጥበባውያኑ "የሰዎች ልጆች" ጭምር፡ በሚጠቅም መንገድ፡ ተዘጋጅቶ ሊቀርብ በተቻለ ነበር።

እኒህ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ኪዳናዊ የኾነውን፡ የራሳቸውን፡ "የቀን አቈጣጠር ሥርዓት" የሰዎች ልጆች ከኾነው፡ ከተስማሚው ጋር በማዛመድ፡ በዚችው፡ በጳጒሜ ሰሞን አዘጋጅተው የሚያቀርቡበት፥ እርሱንም ተከትለው የሚሠሩበት ምክንያት አላቸው፤ ይህም፡ በእነዚሁ ኅብረተሰቦች መካከል፡ በምድራዊው ዓለምና በሥጋዊው ህልውና፡ ዐብረው የሚኖሩ በመኾናቸው፡ ኪዳናዊ ለኾነው፡ ለዚሁ የኢትዮጵያዊነት ሕይወታቸውና ህልውናቸው፡ መመሪያ ኾኖ እንዲያግዛቸው ለማድረግ ያህል እንጂ፡ አስፈላጊነቱ፡ ከዚህ ያለፈ ኾኖ በመገኘቱ አለመኾኑ፡ ሊታወቅ ይገባል።

አዎን! "የኢትዮጵያ ልጆች"፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው፥ በመለኮታዊዉም ሥነ ተፈጥሮአቸው ምክንያት፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም፡ ከእግዚአብሔር አብወእም በመወለዳቸው፡ ከነጋሢነታቸው እና ከካህንነታቸው ጋር፡ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው።

ከዚህ የተነሣ፡ እኒሁ የእግዚአብሔር ልጆች፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ውስጥ፡ ከላይ እንደተጠቀሰው፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ምሥዋዐ-መድኃኒትነት እና በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ የሰላመ መስቀሉ ቤዛነት በተገኘችው፡ በቅድስቲቱ የትንሣኤ ሕይወት እና በዘለዓለማዊቷ የሰንበት ዓለም፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የእውነት አምልኮ፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም፡ ፍጹም ኹለንተናዊ በኾነው ህልውናቸው የሚኖሩ ናቸው።

ስለዚህ ነው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታቸው ጸንተው ለሚኖሩት፡ "ለእግዚአብሔር እና ለኢትዮጵያ ልጆች"፡ "የሰው ልጆች!" የሠሩት፡ የጊዜ መሥፈሪያና መቍጠሪያ ሥርዓት የማያስፈልጋቸው። ይህ እውነታ፡ በኪዳናውያትና በኪዳናውያን ዘንድ፡ እንዳይዘነጋ ያስፈልጋል። አዎን! እነርሱ፡ በዚህ ኪዳናዊ ሕይወታቸውና ህልውናቸው፡ ሰዓታትንና ቀናትን፥ ሳምንታትንና ወርኃትን፥ ዓመታትንና ዘመናትን መቍጠር አያስፈልጋቸውምና።

እንዲህ ካልኾነ፡ ታዲያ! ስለፈጣሪያችንና አባታችን፡ ስለእግዚአብሔር አብ፥ ስለመድኃኒታችንና እናታችን፡ ስለእግዝእተብሔር እም ኢትዮጵያም፥ እንዲሁም፡ ስለእኛ፡ ስለቅዱሱ ኪዳን ልጆቻቸው፡-

**"አንተሰ፡ አንተ ክመ! ወዓመቲከኒ ዘኢየኀልቅ! ደቂቀ አግብርቲከ ይነብርዋ! ወዘርዖሙኒ ለዓለም ይጸንዕ።**

"አንተ ግን፡ ምንጊዜም፡ ያው አንተው ነህ! ዓመቶችህም፡ ከቶ አያልቁም! የቅዱሱ ኪዳን ልጆችህና ነጋሚዎችህ፣ አገልጋዮችህም፡ በእነዚሁ፡ በማያልቁት ዘመኖችህ፡ ይኖሩባቸዋል፤ ዘራቸውም፥ ትውልዳቸውም፡ ለዘላለም ይጸናል!" ለምን ተባለ!?

እንግዴህ፡ የእግዚአብሔር ቃል፡-

**"ወጽድቁሰ ለእግዚአብሔር፡ ይሄሉ ለዓለም!**

"የእግዚአብሔር እውነት ግን፡ ለዘላለም ይኖራል!" ብሏልና፡ በዚህ ረገድ የተነገረው፡ ይህም የእግዚአብሔር እውነት፡ ለእኛ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻቸው፡ በእርግጥ ይጸናልናል።[፭]

---

[፩] ኪ. ወ. ክ. መጽሓፈ ሰዋስው ወግስ፥ ወመዝገበ ቃላት ሓዲስ፤ ገጽ ፱፻፫።

[፪] ዘፍጥ. ፮፥፩-፬። አሞ. ፱፥ ፯።

[፫] መዝ. ፸፫ (፸፬)፥ ፲፪-፲፬። ዮሓ. ፩፥ ፳፱ እና ፴፮። ራእ. ፳፩፥ ፳፪-፳፯።

[፬] ዘፍጥ. ፮፥ ፫-፲፪፤ ፲፩፥ ፩-፱፤ ዮሓ. ፰፥ ፴፬-፵፯። ራእ. ፲፪፥ ፩-፲፯።

[፭] መዝ. ፩፻፩፥ ፳፯-፳፰። ፻፲፮።

\+ \+ \+